የሚኒስትሮች ም/ቤት **ህዳር 5 ቀን 2011 ዓ.ም** ባካሄደው ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ የሚከተሉትን ውሳኔዎችን አሳልፏል፡

1. ምክር ቤቱ በቀረበው የብሄራዊ ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡ ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በተለያዩ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ግጭቶች ምክንያት በህዝቦች መካከል የተደራረቡ የቁርሾ ስሜቶችን ለማከም እውነትና ፍትህ ላይ መሰረት ያደረገ እርቅን ለማዉረድ ያግዛል፡፡
2. ቀጥሎ ምክር ቤቱ የማንነትና አስተዳደር ወሰን ጉዳዮች ኮሚሽንን ለማቋቋም በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡ ኮሚሽኑ በክልሎች የአስተዳደር ወሰንና በማንነት ጥያቄዎች ዙሪያ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮችን አገር አቀፍ በሆነና በማያዳግም መንገድ መፍታት፤ ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ውዝግቦች በተለያዩ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል የቅራኔ ምንጭ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ግጭቶች ከፍተኛ ለሆነ አለመረጋጋት መንስኤ ስለሆኑ ለነዚህ ችግሮች ገለልተኛ በሆነ ከፍተኛ ሞያዊ ብቃት ባለውና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ማፈላለግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ነዉ፡፡
3. በሶስተኛ ም/ቤቱ ለልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የሚውል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡
4. በመጨረሻም ም/ቤቱ መንግስት በቅርቡ ያደረገውን ለውጥ ተከትሎ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የተደራጁትን የኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፣ የውሃ ልማት ኮሚሽን፣ የመስኖ ልማት ኮሚሽን፣ የተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን ፣የቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት እና የጂኦ ስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ስልጣን፤ ተግባር እና አደረጃጀትን ለመወሰን ተዘጋጅተው በቀረቡት ረቂቅ ደንቦች ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ደንቦቹ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡና በስራ ላይ እንዲውሉ ም/ቤቱ ወስኗል፡፡